**የትውልድ ጥሪ ለኢትዮጵያ** : **ዳላስ ቴክሳስ**

***ጋዜጣዊ መግለጫ***

በዳላስ የሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የተመሰረተው ***የትውልድ ጥሪ ለኢትዮጵያ*** በመባል የሚታወቀው አካባቢ- በቀል ማህበር ያዘጋጀው ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተገኙበት ስብሰባ በህዳር 10፣2004 ዓ ም በዳላስ ከተማ በ***ደብል ትሪ*** ሆቴል በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል:: ተሰብሳቢዎቹ የህወሃት/ ኢህአዴግ መንግስት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚያደርሰውን ግፍ በተመለከተ በሰፊው ተወያይተዋል:: በተለይ በቅርቡ እስክንድር ነጋ: አንዷለም አራጌ: ርእዮት አለሙና ውብሸት ታዬን የመሳሰሉ ጋዜጠኞች: የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና የሰብአዊ መብት ታጋዮች መታሰራቸውን ጉባዔው አጥብቆ ኮንኗል::

በስብሰባው ላይ የተገኙት ተሳታፊዎች ነፃነቴ ተገፎ ከምኖር ሞት ይሻለኛል በማለት በራሱና በወገኑ ላይ የሚደርሰውን ግፍ አላይም ብሎ እራሱን በእሳት አቃጥሎ የሞተውን የኔሰው ገብሬን በተለየ ሁኔታ ዘክሮታል:: ***የትውልድ ጥሪ ለኢትዮጵያ*** የኔሰው የሞተለት ነፃነትና ዲሞክራሲን በኢትዮጵያ ውስጥ የማየት ህልም እስኪሳካ ድረስ ትግሉን የመቀጠል ጥረቱን አጠናክሮ እንደሚገፋበት ቃል ይገባል::

ይሄው ***የትውልድ ጥሪ ለኢትዮጵያ*** ያዘጋጀው ስብሰባ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ እንደ እነ ጀነራል አሳምነው: ዋቢ ሃጂ: አበራሽ በርታ: ደብተራው:ጌቱ ቡሽራ እና ሌሎች በሺዎች የሚቆጠሩ በስልጣን ላይ ባለው መንግስት እስር ቤቶች የሚማቅቁ የፖለቲካ እስረኞችን አስቧቸዋል:: ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ከእስር እንዲፈቱም ጥሪ አስተላልፏል:: ከዚህ በላይ ግን ማንም በፖለቲካ እምነቱ ምክንያት የማይታሰርባት: የማይሳቀቅባትና በአጠቃላይ ችግር ላይ የማይወድቅባት ኢትዮጵያን ለመገንባት ሁላችንም እንድንተጋ ***የትውልድ ጥሪ ለኢትዮጵያ*** ወገናዊ ጥሪውን ያቀርባል::

የስብሰባው ተሳታፊዎች በጥልቀት ከተወያዩ በኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ አምባገነንነትን ለአንዴዬና ለመጨረሻ ግዜ ከኢትዮጵያ ምድር ለማጥፋት እና ዘለቄታነት ያለው ዲሞክራሲ ለመገንባት የሚያደርገውን ትግል ለማገዝ ያላቸውን ቁርጠኝነት ገልፀዋል:: በተጨማሪም ***የትውልድ ጥሪ ለኢትዮጵያ*** ኢትዮጵያውያን በያሉበት አካባቢ ተደራጅተው መታገል ወሳኝ መሆኑን በማመን በዳላስ ፎርትወርዝና እና አካባቢው የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ለትግሉ የማስተባበር ስራውን ከመቼውም የበለጠ አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን በድጋሚ ያረጋግጣል::

የኢትዮጵያ ህዝብ በህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት የሚደርስበትን ግፍና ኢፍትሃዊነት እንዲሁም ሃገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበትን አደገኛ ሁኔታ እያጋለጥን ለህዝብ እናሳውቃለን::እንደአካባቢ በቀል ማህበርነቱ ***የትውልድ ጥሪ ለኢትዮጵያ*** ከሌሎች ተመሳሳይ አላማ ካላቸው በዳላስም ሆነ ከዳላስ ውጪ ከሚንቀሳቀሱ ኢትዮጵያዊያን ማህበራት ጋር ተቀራርቦና ተቀናጅቶ መስራት አስፈላጊ መሆኑን ያምናል:: ለዚህም ጠንክሮ ይሰራል::

በመጨረሻም ***የትውልድ ጥሪ ለኢትዮጵያ*** አባላት ባለፉት 50 እና 60 ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህና ነፃነት እንዲሰፍን በመጠየቃቸው አሁን ስልጣን ላይ ባለው መንግስትና በቀደሙት መንግስታት ጭምር የተገደሉ: የታሰሩና: የተሰደዱ ኢትዮጵያውያንን ለማስታወስ በታህሣስ 1 ቀን 2004 ዓ.ም የሻማ ማብራት ስነስርአት ለማድረግ ተስማምተዋል:: የከፈላችሁትን መስዋዕትነት ምን ግዜም አንረሳውም እንላቸዋለን:: ለኢትዮጵያ ያላችሁ ህልም እስከሚሳካ ድረስ ትግላችንን አናቆምም::

ከተባበርን እናሸንፋለን!!

***የትውልድ ጥሪ ለኢትዮጵያ** ዳላስ, ቴክሳስ፣ ህዳር 10: 2004 ዓ.ም::*

***Yetwuld Tiri for Ethiopia*, Dallas, Texas.**

***Press Release***

Ethiopians and Ethiopian Americans residing in Dallas Fort worth area held a successful meeting organized by ***Yetwuld Tiri for Ethiopia*** on November 20, 2011 at Double Tree Hotel, Richardson, Texas. The participants discussed in length the suffering of the Ethiopian people and the gross human rights violations perpetrated by the TPLF/EPRDF regime. In particular, the meeting condemned the arrest of political leaders, democracy activists and journalists such as Eskinder Nega, Woubshet Taye, Reiot Alemu, Andualem Arage etc.

The participants paid a special tribute to Yenesew Gebre, the Bouazizi of Ethiopia, who recently burned himself to death protesting the out-of-control abuse of human and democratic rights in Ethiopia. ***Yetwuld Tiri for Ethiopia*** vowed to continue its effort until justice and democratic rights are a reality in Ethiopia, a cause for which Yenesew died.

The meeting also paid tribute to other political prisoners like General Asaminew, Wabi Haj, Aberash Berta, Debtraw, Getu Bushura, and thousands of others languishing in the regime's notorious jails. We call for the immediate release of all political prisoners. More important, we are committed to contribute our part towards the struggle for building an Ethiopia in which no Ethiopian will be arrested, tortured or in any way suffer because of his/her political views.

After a thorough discussion, Participants expressed their resolve to support the Ethiopian people's struggle to end dictatorship once and for all and establish a lasting democracy in our country. The gathering also stressed the importance of local and grass root organizing and members voiced their determination to mobilize the Ethiopian diaspora in the Dallas-fort worth area for the struggle.

The meeting also reaffirms its commitment to intensify the effort to expose the injustice and the suffering of the Ethiopian people as well as the dangerous situation our country faces under the TPLF/EPRDF regime. As a local, grass root movement, ***Yetwuld Tiri for Ethiopia*** recognizes the urgent need to coordinate efforts with similar groups both here in Dallas as well as outside, and promises to do everything it can towards that end.

Finally, the gathering decided to organize a candle vigil on December 11, 2011 at Double Tree Hotel, Richardson Texas, in memory of all Ethiopians killed, jailed, tortured and exiled in the last 5 to 6 decades, both by the current as well as previous regimes because they have the courage to dream justice, democracy and the rule of law in Ethiopia. We want to tell them: we will never forget your sacrifice. We will not rest until your dream is realized in our country.

UNITED WE WIN!!!

***Yetwuld Tiri for Ethiopia***, Dallas Texas, November 20, 2011.